# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዜና መጽሄት

# Debre Markos University Newsletter

በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት በየወሩ የሚታተም

Monthly Newsletter Published by the Corporate Communications Directorate

ቅጽ-3 ቁጥር-26 ሰኔ ወር 2007 ዓ.ም እትም Volume-3 Number-26 June 2015 G.C Release

የአንድን ሀገር ልማት ለማፋጠንና የዲሞክራሲ ስርአትን ለማስፋት ዋናው ቁልፍ መሳሪያ ትምህርት .................................... 3

የሚገነባው የጤና ሳይንስ ኮሌጅ በየቦታው ተበታትኖ የሚማረውን የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪ በአንድ ካምፓስ በማስተማር ውጤታማ ስራ ለመስራትና ዘመናዊ የመማሪያ ሆስፒታል በመገንባት ትልቅ ሀገራዊ ግብ ማሳኪያም ..............................................6

ቅርሶቻችንን ተንከባክበን ለሌላው አለም በማስተዋወቅ ረገድ ብዙ ጕብኝዎችን በተገቢው ................................. 7

ዩኒቨርሲቲው ለአካባቢው ማህበረሰብ ከመደበኛው የትምህርት መርሀ ግብር በተጨማሪ በክረምትና በማታው መርሀ ግብር ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው ሳይርቁ በአቅራቢያቸው እንዲማሩ በማድረጉ .................................... 9

## በውስጥ ገፆቻችን

- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለ7ኛ ጊዜ ተማሪዎችን በደማቅ ሁኔታ አስመረቀ.............................. 2
- የደብር ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን ለማስገንባት ከሀንፃ ተቋራጭ ድርጅቶች ጋር የውል ስምምነት ተፈራረመ ................................ 5
- በቅርስ አያያዝ አጠባበቅና አመዘጋገብ ዙሪያ ስልጠና ተሰጠ .................................... 7
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከከተማው ማህበረሰብ ጋር ተወያዬ --------------------- 9
- የፈጠራና ልዩ ችሎታ ማበልፀጊያ ማዕከል ለማቋቋም የምክክር መድረክ ተካሄደ......... 11
- የአስተዳደር ህንፃና የመምህራንና ሰራተኞች መዝናኛ ለማስገንባት የሚያስችል ስምምነት ተፈረመ ..... 13
- በሴት ተማሪዎች ላይ በሚታዩ ችግሮች እና የመፍትሄ ሃሳቦች ዙሪያ ውይይት ተደረገ.......15
- የህግ ትምህርት ቤት ለፍትህ አካላት ስልጠና ሰጠ ...... 17



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

## ራዕይ
## Vision

እ.ኤ.አ. በ2030 ከዓለም ካሉ ታዋቂ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ሆኖ መገኘት፡፡

**Debre Markos University aspires to be world class University in 2030.**

## ተልዕኮ
## Mission

ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ማፍራት

**Producing competent and innovative professionals through providing quality instructional, CoCurricular and cultural involvement.**

አጋር አካላትን በማሳተፍ ችግር ፈች ጥናትና ምርምር ማድረግ፣

Carrying out problem solving research through the active involvement of stakeholders and,

ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የማማከርና የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ለሃገራችን ልማት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ፣

Providing demand driven community and consultancy services.



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለ7ኛ ጊዜ ተማሪዎችን በደማቅ ሁኔታ አስመረቀ

ሙሀመድ ሰኢድ

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በመደበኛውና በማታው መርሃ ግብር ያሰለጠናቸውን 2765 ተማሪዎች በደማቅ ሁኔታ አስመረቀ፡፡







ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ለተመራቂ ተማሪዎች ንግግር ሲያደርጉ

በምረቃ ስነ ስርዓቱ ላይ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ ባደረጉት ንግግር ትምህርት ለሀገር ግንባታ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ በመግለጽ ሀገራችንም ባለፉት ዓመታት የትምህርትን ፍትሃዊነት፣ ጥራትና ተገቢነት ጠብቆ ለማስፋፋት ጥረት ሲደረግ መቆየቱን ጠቁመዋል፡፡ በዚህም በአለፉት ስርዓቶች ሀገራችን የኋላቀርነት ተምሳሌት ሆና የቆየች ቢሆንም መንግስት ባደረገው ያላሰለሰ ጥረት ዕምርታ ያለው ለውጥ ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

እንደ ዶ/ር ጥላዬ ገለፃ መንግስት ይህን ችግር ለመቅረፍ ከ1987 ጀምሮ ምላሽ ሰጪ የሆነ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ቀርፆ ከፍተኛ ርብርብ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በዚህም ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ1999 ዓ.ም. በ53 መምህራን፣ በ34 ቋሚና በ21 ኮንትራት ሰራተኞች በስምንት የትምህርት ክፍሎች ስራውን እንደጀመረ አስታውሰው በአሁኑ ሰአት በስድስት ኮሌጆችና አንድ ትምህርት ቤት በ38 የቅድመ ምረቃና በ13 የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች 11,000 በመደበኛው፣ 6661 በክረምቱ እና 4831 በማታው በድምሩ 23,101 በላይ ተማሪዎችን እያስተናገደ ነው፡፡

የመምህራንና ሰራተኞች ቁጥርም በቡሬና በዋናው ግቢ 988 መምህራንና 1073 አስተዳደር ሰራተኞች እንዳሉት ገልፀዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው በ2007 ዓ.ም. 1973 ወንድ እና 792 ሴት በድምሩ



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

2765 ተማሪዎችን እንደአስመረቀ እና የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የተቀመጠውን የሴት መምህራንን ቁጥር ለማሳደግ 66 ሴት ተመራቂዎችን በመምህርነት ማስቀረቱን ገልፀዋል፡፡ በቀጣይም በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መጨረሻ 20,000 ተማሪዎች ለመቀበል ግምቱ አንድ ቢሊዮን በሚጠጋ ካፒታል በጀት የማስፋፊያ ግንባታ መጀመሩን ገልፀዋል፡፡

የእለቱ የክብር እንግዳ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክትል ኃላፊ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ እና የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ክቡር አቶ ብናልፍ አንዷለም እንደገለፁት የአንድን ሀገር ልማት ለማፋጠንና የዲሞክራሲ ስርአትን ለማስፋት ዋናው ቁልፍ መሳሪያ ትምህርት መሆኑን ገልፀው ሀገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ሌት ከቀን ባደረገችው ርብርብ ስኬታማ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ በዚህም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ለማዳረስ የተቀመጠውን የምዕተ ዓመቱን ግብ ካሳኩ አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ውጤት አስመዝግባለች፡፡




ክቡር አቶ ብናልፍ አንዷለም ለተመራቂዎች የስራ መመሪያ ሲሰጡ

የከፍተኛ ትምህርትን በማስፋፋትም ረገድ ረጅም ርቀት መጓዟን ገልፀዋል፡፡ በመጨረሻም ተመራቂ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ህይወታቸው ውጭ በቀጣይም ከተሞክሯቸው እንዲማሩና ወገናቸውን በጽናትና በታማኝነት እንዲያገለግሉ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በምረቃ በዓሉ ላይ ከኦስትሪያ ቦኩ ዩኒቨርሲቲ የተጋበዙት የምርምርና አለማቀፍ የምርምር ትብብር ምክትል ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ዶ/ር ጆሴፍ ግሎስሊል የተገኙ ሲሆን ለበዓሉ ታዳሚዎች



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

ዩኒቨርሲቲያቸው ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በትብብር ለመስራት የጋራ ስምምነት መፈረሙን አስታውሰው ለተግባራዊነቱ ዝግጁ መሆኑን በንግግራቸው አረጋግጠዋል፡፡

በምረቃ በዓሉ ላይ የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮ በተሳለጠ መልኩ ከግብ እንዲደርስ ለማድረግ ምቹ የትምህርት አካባቢ ከመፍጠር አንፃር ዩኒቨርሲቲውን ቅጥር ግቢ ሳቢና ማራኪ ለማድረግ ባደረጉት ከፍተኛ እንቅስቃሴና ግቢው ማራኪ ገጽታ እንዲኖረው ላደረጉት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የግቢ ውበትና ጽዳት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ግርማይ የዕለቱ ልዩ ተሸላሚ መሆናቸው ተጠቁሟል፡፡ በዚህም የዩኒቨርሲቲው ልዩ ተሸላሚ መምህር ሰለሞን ግርማይ የተዘጋጀለትን ሞተር ብስክሌት ከዕለቱ የክብር እንግዳ ክቡር አቶ ብናልፍ አንዱአለም እጅ ተረክቧል፡፡ አቶ ሰለሞን ግርማይ በበኩላቸው የሰሩት ስራ የሚያረካቸውና በእውነትም ተጨባጭና ትርጉም ያለው ለውጥ ያዩበት መሆኑን ጠቁመው ዩኒቨርሲቲው ያበረከተላቸው ሽልማት ከዚህ በበለጠ እንዲሰሩ እንደሚያነሳሳቸው ገልፀዋል፡፡





አቶ ሰለሞን ግርማይ ሽልማታቸውን ከክብር እንግዳው ክቡር አቶ ብናልፍ እጅ ሲቀበሉ

በመጨረሻም ከየኮሌጁ ከአንድ እስከ ሶስት የወጡ ተማሪዎች የሰርተፊኬት፣ ከየኮሌጁ አንደኛ የወጡ ተማሪዎች የሜዳሊያ እና ከአጠቃላይ ተመራቂ የወርቅ ተሸልመዋል፡፡



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

# የደብር ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን ለማስገንባት ከህንፃ ተቋራጭ ድርጅቶች ጋር የውል ስምምነት ተፈራረመ

በሰለሞን አበበ



የደ/ማ/ዩ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ የውል ስምምነቱን ሲያካሂዱ

**ደ/ማ/ዩ፡-** የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በደብረ ማርቆስ ከተማ እና በቡሬ ካምፓስ የሚያሰራቸውን የማስፋፊያ ፕሮጀክቶች ለማስገንባት ከሶስት ኮንስትራክሽን ድርጅቶች ጋር የውል ስምምነት ተፈራርመ፡፡ ከስምምነት መርሃ ግብሩ መረዳት እንደተቻለው ዩኒቨርሲቲው ከዩቴክ ኮንስራክሽን ጋር ሎት አንድን በ362,654,295.15 ብር (ሦስት መቶ ስልሳ ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃምሳ አራት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና አምስት ብር ከአስራ አምስት ሳንቲም)፣ ከአፍሮ ጽዮን ኮንስትራክሽን ጋር ሎት ሁለትን በ332,359,258.31 ብር (ሶስት መቶ ሰላሳ ሁለት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺ ሁለት መቶ ሃምሳ ስምንት ብር ከሰላሳ አንድ ሳንቲም) እንዲሁም ከስሪኤም እንጅነሪንግ ጋር ሎት ሦስትን በ264,472,526.36 ብር (ሁለት መቶ ሰላሳ አራት ሚሊዮን አራት መቶ ሰባ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ስድስት ብር ከሰላሳ አንድ ሳንቲም) በሆነ የፕሮጀክት ዋጋ ለማሰራት የውል ስምምነት ተፈራርሟል፡፡



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

በውል ስምምነት መርሀ ግብሩ ላይ የደብር ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ ዩኒቨርሲቲው ያለበትን ሁኔታ፣ የፕሮጀክቱን አስፈላጊነት፣ ሊያጋጥሙ በሚችሉ ችግሮችና የመፍትሄ አቅጣጫቸው፣ በግንኙነት

ስርዓቱ ላይ እንዲሁም ከአሰሪው የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ ከአማካሪው ድርጅት እና ከህንፃ ተቋራጮች የሚጠበቀውን እያንዳንዱን ጉዳይ እና የተጠያቂነት ስርዓት በማስማፈን ዙሪያ ገለፃ አድርገዋል፡፡

እንደ ዶ/ር ጥላዬ ገለፃ ዩኒቨርሲቲው በሁለተኛው የእድገትና ትራስፎርሜሽን ዘመን የመደበኛ ተማሪዎችን ቁጥር ሃያ ሽህ ለማድረስ ግብ ይዞ እየሰራ እንደሚገኝ ገልፀው በደብረ ማርቆስ ከተማ ለሚገነባው የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሰላሳ ሚሊዮን ብር የቦታ ካሳ ክፍያ በመክፈል እና የአንድ መቶ ሀምሳ ሁለት ሄክታር መሬት ከደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር በመረከብ የግንባታ ስራውን በአፍሮ ጽዮን ኮንስትራክሽን እና በስሪ ኤም ኢንጅነሪንግ ለማከናወን ተስማምቷል፡፡ በተጨማሪም በቡሬ ካምፓስ የሚገነባውን የማስፋፊያ ግንባታ ለማሰራትም ከዩቴክ ኮንስትራክሽን ጋር ውል ተፈራርሟል፡፡

በደብረ ማርቆስ ከተማ የሚገነባው የጤና ሳይንስ ኮሌጅ በየቦታው ተበታትኖ የሚማረውን የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪ በአንድ ካምፓስ በማስተማር ውጤታማ ስራ ለመስራት ይረዳዋል ያሉት ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ ፕሮጀክቱ ዘመናዊ የመማሪያ ሆስፒታል በመገንባት ትልቅ ሀገራዊ ግብ ማሳኪያም መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል፡፡ እንደ ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ ይህ ፕሮጀክት የመጀመሪያው ፌዝ ግንባታ (ሎት አንድ፣ ሎት ሁለት እንዲሁም ሎት ሦስት የግንባታ ሂደቶችን እንደያዘ ጠቁመው በቀጣይም የመጀመሪያው ፌዝ ግንባታ ሲጠናቀቅ ወደ ሁለተኛው ፌዝ እና ሦስተኛው ፌዝ የግንባታ ምዕራፎች ዩኒቨርስቲው እንደሚሸጋገር ጠቁመዋል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ተስፋሁን አበበ በበኩላቸው እንደገለፁት የመጀመሪያው ፌዝ የግንባታ ሂደት በሎት አንድ፣ ሎት ሁለት እና ሎት ሦስት የሚሰሩት ባለ 4 ፎቅ የተማሪ መኖሪያዎች፣ መማሪያ ክፍሎች፣ ቤተ መጽሐፍት፣ ላብራቶሪዎች፣ ካፍቴሪያ፣ የምግብ ማብሰያ፣ የአስተዳደር ህንፃዎች እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡ በዚህም በደብረ ማርቆስ ከተማ የሚገነባው የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የመጀመሪያው ምዕራፍ ግንባታ ሲጠናቀቅ በሎት ሁለት እና በሎት ሦስት ግንባታዎች 7000 (ሰባት ሺህ) ተማሪዎችን የማስተናገድ አቅም እንዳለውና በቡሬ ካምፓስ

በዚሁ ምዕራፍ የሚገነባውም ከ3000 (ሦስት ሺህ) በላይ ተማሪዎችን የማስተናገድ አቅም እንደሚኖረው እና ግንባታዎችም በአንድ አመት ከ6 ወራት ውስጥ እንደሚጠናቀቁ እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የማስፋፊያ ግንባታ በፌዝ ሁለት እና በፌዝ ሶስት በቀጣይ የዘመናዊ የማስተማሪያ ሆስፒታል፣ የስፖርት ስቴዲየም እና ለተማሪዎች መዝናኛ የሚያገለግሉ ህንፃዎች ባለቤት እንደሚሆን ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል፡፡

## በቅርስ አያያዝ አጠባበቅና አመዘጋገብ ዙሪያ ስልጠና ተሰጠ

በሰለሞን አበበ




ዶ/ር ስማቸው ጋሻዬ የደ/ማ/ዩ ምር/ማህ/አገ/ም/ፕሬዚዳንት ስልጠናውን በንግግር ሲከፍቱ

**ደ/ማ/ዩ፡-** የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ህዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም የቤተ መዛግብት ማዕከል ከምስራቅ ጐጃም ዞን የተለያዩ ወረዳዎች ለመጡ የቅርስ ባለሙያዎች፣ ፖሊስ ጽ/ቤት ኃላፊዎች እና የሀይማኖት አባቶች ስለ ቅርስ አያያዝ፣ አጠባበቅና አመዘጋገብ የሁለት ቀናት ስልጠና ሰጠ፡፡

ስልጠናውን በንግግር የከፈቱት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ስማቸው ጋሻዬ እንዳሉት ዩኒቨርሲቲው በተደራጀ መልኩ አይሁን እንጅ በቅርስ አያያዝና አጠባበቅ ዙሪያ ጥናቶችን ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ከመማር ማስተማሩ ጐን ለጐን ምርምር በማድረግ የማህበረሰቡን ችግር የመፍታት፣ የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

እንዲሁም ባህላዊ እሴቶችን የመመርመር የማጥናት እና እንዲጠበቁ የማድረግ ሀላፊነት አለበት፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ አልተጠቀምንበትም እንጅ የበርካታ ተፈጥሯዊ፣ ባህላዊና ሰው ሰራሽ ቅርስ ያላትና የእነዚህ ሁሉ ቅርሶች ባለፀጋ አገር መሆኗን ያወሱት ምክትል ፕሬዚዳንቱ የሚጠበቀውን ያህል ስላልሰራን ቅርሶቻችንን ተንከባክበን ለሌላው አለም በማስተዋወቅ ረገድ ብዙ ጉብኝዎችን በተገቢው

መንገድ መሳብ አልቻልንም ብለዋል፡፡ ስለሆነም ከዚህ ስልጠና በኋላ በየአካባቢው ተግባራዊ የሆነ የቅርስ እንክብካቤ፣ አያያዝና ምዝገባ በማድረግ ቅርሶቻችንን ማልማት ይጠበቅብናል በማለት አሳስበዋል፡፡

እንደ አቶ ግዛቸው አንዳርጌ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ሃዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም የቤተ መዛግብት ማዕከል ኦፊሰር ገለፃ የስልጠናው አላማ በዞናችን የሚገኙ በርካታ የቅርስ ክምችቶችን በመመዝገብ፣ በመያዝና በመንከባከብ እንዲሁም ሙዚየሞችን በማደራጀት ዙሪያ ያለውን ክፍተት ለመሙላት ነው ብለዋል፡፡

በስልጠና መርሀ ግብሩ የቅርስ ትርጉም፣ አይነትና ጠቀሜታ የሚል ጽሁፍ በዩኒቨርሲቲው የታሪክና ቅርስ አስተዳደር ትምህርት ክፍል መምህር አቶ ይሂይስ አረጉ፣ የቅርስ ምዝገባ የሚል የስልጠና ርዕስ በአቶ ተስፋዬ አስናቀው ከፌዴራል ቅርስ ጥናትና ምዝገባ ባለስልጣን፣ የቅርስ አያያዝና አጠባበቅ የሚል የስልጠና ጽሁፍ በአቶ ግዛቸው መንግስቱ ከአማራ ክልል ባህል ቱሪዝም ቢሮ የቅርስ አስተዳደር የስራ ሂደት እንዲሁም የተንቀሳቃሽ ቅርሶች ልማት የሙዚየም አደረጃጀትና አያያዝ የሚል የስልጠና ርዕስ ከብሄራዊ ሙዚዬም ከመጡት በአቶ በረከት ዘውዱ ቀርቦ ሰልጣኞች ቅርስ ምን እንደሆነ፣ ምን አይነት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ እንዳለው፣ የቅርስ አመዘጋገብ ዘዴዎች እንዲሁም ቅርሶቻችንን እንዴት እንደምንይዝና እንደምንጠብቅ ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በተጨማሪም ተንቀሳቃሽ ቅርሶች እንዴት እንደሚለሙ ሙዚየም እንዴት እንደሚደራጅና እንደሚያዝም ሰፊ ገለፃ ተደርጎላቸው ሰልጣኞች የቅርስ አመዘጋገብ የተግባር ልምምድ በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት አድርገዋል፡፡

በስልጠናው ላይ ሲሳተፉ ያገኘናቸው ከጠቅላይ ቤተ ክህነት የህግ አገልግሎት መምሪያ የመጡት ምክትል ኃላፊው መምህር አባ ገብረስላሴ ጌትነት እንዳሉት ቅርስ ማለት የማንነት መገለጫ፣



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

ትናንትን የምናይበትና ለነገ የምንማርበት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንም የቅርስን ምንነት ስለምታውቅ በባለቤትነት የምታስተዳድር እና የምትንከባከብ ልዩ ጥበቃም የምታደርግ የሐይማኖት ተቋም ናት፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን መንግስት ዘመናዊ ምዝገባን ከማምጣቱ በፊት በሯሷ መዋቅር በባህላዊ መልኩ ቅርስን ስትመዘገብ ቆይታለች ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መንግስት አዋጆችንና መመሪያዎችን አውጥቶ ወደ ምዝገባ ሲገባ በልዩ ልዩ ቦታ

የሚገኙትን ቅርሶቿን ለምዝገባ በማዘጋጀት፣ የቅርስ ምዝገባ ባለሙያዎችም ለሚያቀርቡት ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ በመስጠትና ለቅርስ ምዝገባው ልዩ ድጋፍ በማድረግ በአሁኑ ሰአት ቅርሶችን በስፋት እያስመዘገበች ትገኛለች ብለዋል፡፡

## የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከከተማው ማህበረሰብ ጋር ተወያዩ

በሰለሞን አበበ



አቶ ምስጋናው ጋሻው የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ውይይቱን ሲመሩ

**ደ/ማ/ዩ፡-** የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከከተማው የንግድ ምክር ቤት አባላት፣ ከነዋሪ ተወካዮች፣ ከሀይማኖት ተቋማት መሪዎች እና ከከተማው የፀጥታ አካላት ጋር በዩኒቨርሲቲው እንቅስቃሴ እና የማህበረሰቡ ግንኙነት ዙሪያ በደብረ ማርቆስ ከተማ ሲኒማ አዳራሽ ተወያዩ፡፡

በውይይቱ መርሀ ግብር ላይ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ምስጋናው ጋሻው ወቅታዊ የዩኒቨርሲቲውን እንቅስቃሴ የሚያስቃኝ የመነሻ ጽሁፍ



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

አቅርበዋል፡፡ በቀረበው ጽሁፍም ዩኒቨርሲቲው በሁለት ካምፓስ በሠባት ኮሌጆችና በሰላሳ ስምንት ትምህርት ክፍሎች ከሁለት ሺህ የሚበልጡ ሰራተኞችና ከሃያ አምስት ሺህ በላይ ተማሪዎችን እያስተማረ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው ለአካባቢው ማህበረሰብ ከመደበኛው የትምህርት መርሀ ግብር በተጨማሪ በክረምትና በማታው መርሀ ግብር ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው ሳይርቁ በአቅራቢያቸው እንዲማሩ በማድረጉ ተመራጭ የትምህርት ተቋም ሁኗል ብለዋል፡፡

ዳይሬክተሩ በውይይት መነሻ ጽሁፋቸው የዩኒቨርሲቲውን የምርምር ስራዎች እንቅስቃሴ፣ የትብብር እና አጋርነት ስራዎች፣ የቢዝነስና ልማት የስራ አፈፃፀሞች እንዲሁም ሌሎችንም ተያያዥ ጉዳዮች ጨምረው በዝርዝር አቅርበዋል፡፡

በውይይት መርሀ ግብሩ ተሳታፊ የሆኑ የከተማው ማህበረሰብ አባላትም የዩኒቨርሲቲውን የትምህርት፣ የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት እንቅስቃሴ አድንቀው የዩኒቨርሲቲው የግዥ ሂደት የከተማውን የንግድ ማህበረሰብ ተጠቃሚ አላደረገም፣ የዩኒቨርሲቲው ኢንተርፕራይዝ ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች የሚሸፍኑት ስራ ላይ ይሰማራል፣ ጨረታ ይሰረዝብናል ወዘተ የሚሉ አስተያየቶችን አቅርበዋል፡፡ የተማሪዎች ስነ ምግባር ሊሻሻል ይገባል ያሉት ነዋሪዎቹ በተለይም አምሽቶ መግባት፣ ስካርና የሱስ ተጠቂ መሆን ይታያል ብለዋል፡፡ ለተነሱት ጥያቄዎችም የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር እና ተማሪዎች ጉዳይ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ደርጃው ፈንቴ በሰጡት ምላሽ ዩኒቨርሲቲው ግዥዎችን በዋናነት ለተማሪዎች የምግብ አቅርቦት የሚፈጽመው በግልጽ ጨረታ መሆኑን ገልፀው ነገር ግን የአካባቢው ነጋዴዎች አካባቢው የሚፈጥርላቸውን ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ በማስገባት እየተወዳደሩ አይደለም ብለዋል፡፡ በተለይም የንግዱ ማህበረሰብ ፕሮፎርማ ሞልቶ እንደማይመልስና የንግዱ ማህበረሰብ የቫት ተመዝጋቢ ያለመሆን ችግር ነጋዴውን ከዩኒቨርሲቲው ግዥ ሙሉ በሙሉ ተጠቃሚ እንዳላደረገው ገልፀዋል፡፡ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ጨምረው እንዳመለከቱት የጨረታ ግዥም ይሁን የፕሮፎርማ ግዥ በገቢያ ጥናት መረጃ የተደገፈ ስለሆነ ዋጋ በማጋነን በጨረታው የሚሳተፍ ነጋዴዎች ጨረታቸው ውድቅ ይሆናል ብለዋል፡፡ የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ ጉዳይም የሚወስነው በሚገዛው የግዥ መጠን ሁኖ ስታንዳርድ እንዳለውም አሳስበዋል፡፡ የተማሪዎችንም ስነ ምግባር ለማስተካከል የቁጥጥር ስርዓቱ የበለጠ እንደሚጠናከር ገልፀው ነገር ግን ከዚያ በላይ መስራት ያለበት አመለካከቱ ላይ መሆን እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ በበኩላቸው እንዳሉት ዩኒቨርሲቲዎች ሲቋቋሙ ከተሰጧቸው ተልዕኮዎች በተጨማሪ የራሳቸውን ገቢ ማመንጨት እንደሚችሉ በህግ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በመነሳት የተቋቋመው የመንቆረር አግሮ ኢንዱስትሪ ኢንተርፕራይዝ ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች ሊሸፍኑት የማይችሉትን ዘርፍ ለመሸፈን መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ስለሆነም ኢንተርፕራይዙ የተቋቋመው በዋናነት የመማር ማስተማሩን ለመደገፍ እንጅ ጥቃቅን እና አነስተኛ ድርጅቶች የሚሰሩትን ስራዎች ለመሻማት አይደለም በማለት ምክትል ፕሬዚዳንቱ ገልፀዋል፡፡

በሌሎች ዘርፎች ለተነሱት ጥያቄዎችም የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ኃላፊ እና ሌሎችም ኃላፊዎች ምላሾችን ሰጥተዋል፡፡

በመጨረሻም የውይይቱን የማጠቃለያ ኃሳብ ያስቀመጡት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ጥላዬ ጌቴ ዩኒቨርሲቲው በቀጣይ ተጨማሪ መድረኮችን በመፍጠር በሁለቱም በኩል የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ እንደሚሰራ አስረድተዋል፡፡ ፕሬዚዳንቱ እንደገለፁት ዩኒቨርሲቲው በማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፉ የነጋዴውን ማህበረሰብ በወቅታዊ የህግና የንግድ አሰራሮች ላይ ስልጠና የሚሰጥ ይሆናል፡፡

## የፈጠራና ልዩ ችሎታ ማበልፀጊያ ማዕከል ለማቋቋም የምክክር መድረክ ተካሄደ

**በሰለሞን አበበ**





ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ የደ/ማ/ዩ/አ/ጉ/ም/ፕሬዚዳንት መድረኩን ሲመሩ እና
ዶ/ር ሀይማኖት ዋሴ የም/ህትመት ዳይሬክቶሬት  የህትመት ኦፊሰር የውይይት መነሻ ጽሁፍ ሲያቀርቡ

**ደ/ማ/ዩ፡-** የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የፈጠራና ልዩ ችሎታ ማበልፀጊያ ማዕከል ለማቋቋም የምክክር መድረክ ከተለያዩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ከአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ የመጡ ኃላፊዎች በተገኙበት አካሄደ፡፡

የምክክር መድረኩን በንግግር የከፈቱት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ስማቸው ጋሻዬ እንዳሉት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲም ከዚህ አስቀድሞ የእግር ኳስ ተሰጥኦ ያላቸውን ልጆች በማሰባሰብ ወደስራው በመግባት አስገራሚ ውጤት አምጥቷል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የክልሉ ትምህርት ቢሮ በአስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት  ተሰጥኦ እና ልዩ ችሎታ ያላቸውን ወጣቶች በማሰባሰብ ስራ መጀመሩን አስረድተዋል፡፡ ልዩ ችሎታ ያላቸው ህፃናት ከተለያየ ቤተሰብ ስለሚገኙ በየትምህርት ቤቶች የመፈለግ ስራ በመስራት ተሰጦአቸውን ከዳር እንዲያደርሱ በጋራ መረባረብ ያስፈልጋል፡፡ ይህ የውይይት መድረክ በዋናነት ልዩ ተሰጥኦ የሚባለውን ከጽንሰ ሀሳቡ ጀምሮ በመረዳት በትምህርት ብቻ ያለውን ልዩ ተሰጥኦ መለየት ሳይሆን ከዚያ ውጭ ያሉ ተሰጥኦዎች ምንድን ናቸው? ይህንንስ ስራ እንዴት እንሂድበት የሚለውን በጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው ለብቻው ችሎታ ማሳደግና ማዳበር አይችልም ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ ባለድርሻ አካላት ትምህርት ቤቶችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በሃሳቡ ላይ በመነጋገር እና በመመካከር የድርሻ ድርሻችንን በመያዝ ወደስራ ለመግባት ያስችለናል በማለት ገልፀዋል፡፡

በውይይት መድረኩ የመነሻ ጽሁፍ ያቀረቡት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ህትመት ዳይሬክቶሬት የህትመት ኦፊሰር የሆኑት ዶ/ር ሃይማኖት ዋሴ እንደሚሉት የዚህ ፕሮጀክት ዋና አላማ ልዩ ችሎታና ፈጠራ ያላቸውን ግለሰቦች ተቋማዊ የሆነ አካባቢ በመፍጠር አቅማቸውን የሚገልፁበት



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

ዕድል መፍጠር ነው፡፡ በዚህም የፈጠራ፣ ልዩ ችሎታና ዕውቀት ያላቸውን ተማሪዎች ተቋማዊ በሆነ መልኩ እንዲመሩ በማድረግ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት አስተዋጽኦ ግንዛቤ ለመፍጠር፣ በዩኒቨርሲቲውና በአካባቢው ህብረተሰብ መካከል የዕውቀት ሽግግር ለመፍጠር፣ ልዩ ፈጠራና ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች ግብአት በማሟላትና በማማከር ለመደገፍ፣ ፈጠራና ልዩ ችሎታን በማበረታታት ለትምህርት ጥራትና ለሀገር እድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በተግባር ለማሳየት እንዲሁም ማዕከሉ የቴክኖሎጂ ማፍለቂያና ማበልፀጊያ እንዲሆን ማስቻል የዚህ ፕሮጀክት አላማዎች ናቸው፡፡

እንደ ዶ/ር ሀይማኖት ዋሴ ገለፃ መንግስት ለትምህርት ጥራት በተለይም ለፈጠራ ሥራ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑ፣ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተለያዩ የፈጠራ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች የሚያበረታታ የውድድር ሲምፖዚየም በመኖሩ እንዲሁም በህብረተሰቡ ተማሪዎች ጥራት ያለው ትምህርት ልጆቻቸው አግኝተው ውጤታማ እንዲሆኑ መፈለጉ የፕሮጀክቱ መልካም አጋጣሚዎች ይሆናሉ ብለዋል፡፡ ዶ/ር ሀይማኖት ፕሮጀክቱን ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን፣ ለፕሮጀክቱ የበጀት ምንጭ ማን እንደሚሆን፣ የፕሮጀክቱን አደረጃጀት እንዲሁም የክትትልና ግምገማ ስርዓት በዝርዝር አቅርበዋል፡፡

በመጨረሻም በቀረበው ጽሁፍ መነሻነትም ተሳታፊዎች የተለያዩ ጥያቄዎችን አቅርበው ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራንም የዚህ ፕሮጀክት ዋነኛ ባለድርሻ አካላት እንደሆኑ አውቀው ወጣቶችን የመለየት የመደገፍና የመኮትኮቱን ስራ ከመቸውም ጊዜ በላይ መስራት እንደሚገባ የቀረበውን ጽሁፍ የመሩት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት አሳስበዋል፡፡

## የአስተዳደር ህንፃና የመምህራንና ሰራተኞች መዝናኛ ለማስገንባት የሚያስችል ስምምነት ተፈረመ

በሰለሞን አበበ






0913-14-96-80
comunication
Facebook: dmu

**ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ የደ/ማ/ዩ/ ፕሬዚዳንት የውል ስምምነቱን ከህንፃ ሥራ ተቋራጭ ድርጅቶች ጋር ሲያካሂዱ**

**ደ/ማ/ዩ፡-** የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ባለፉት ግዜያቶች በተለያዩ ምክንያቶች ዘግይተው የነበሩትን የአስተዳደር ህንፃና የመምህራንና ሰራተኞች መዝኛኛ ለማስገንባት የሚያስችል ስምምነት ከፍሊንት ስቶን ኢንጅነሪንግ እና ታምራት ተመስጌን ኮንስትራክሽን የህንፃ ተቋራጭ ድርጅቶች ጋር የውል ስምምነት ተፈራረመ፡፡

ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት በስምምነት መርሀ ግብሩ ላይ በዩኒቨርሲቲው የጋራ አመራር መኖሩን አውስተው የከፍተኛ አመራሩ የግንባታ ፕሮጀክቶችን በየጊዜው እየገመገመ እንደሚመራቸው ገልፀዋል፡፡ በመቀጠልም ከስራ ተቋራጮች ምን እንደሚጠበቅ፣ ከአማካሪው ከኮንስትራክሽን ስራዎች ድርጅት ምን እንደሚጠበቅና የዩኒቨርሲቲው ፍላጐት ምን እንደሆነ ውይይት ተደርጓል፡፡ እንደ ዶ/ር ጥላዬ እነዚህ ፕሮጀክቶች በባህሪያቸው በጣም መሠረታዊ እና ስትራቴጅካዊ ችግር የሚፈቱ ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ በሁለተኛው ትውልድ የተገነቡት የሀገራችን ዩኒቨርሲቲዎች የአስተዳደር ህንፃና ሌሎች ቢሮዎች እንደሌላቸው አስታውሰው በዩኒቨርሲቲያችን አገልግሎቱ ሲሰጥ የነበረው በኮሌጆችና በትምህርት ክፍሎች ህንፃዎች ላይ ነበር ብለዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ከ2000 /ሁለት ሺህ/ በላይ መምህራን እና ሰራተኞች ያሉበት ተቋም ስለሆነ ከዚህ በፊት ዋናው ማነቆ ሁኖ የቆየው ችግር በእነዚህ ግንባታዎች ይፈታል፡፡ እነዚህ ግንባታዎች የመልካም አስተዳደር መመለሻ ህንፃዎች እንደሚሆኑና ከመንግስት የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም አንፃር ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠሪያ እንደሚሆኑ ፕሬዚዳንቱ ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከኮንስትራክሽን ስራዎች ድርጅት ለአማካሪነት የሚመጡት ባለሙያዎች ግልጽ፣ ችግር የሚፈቱ፣ በሳይቱ ላይ ዕለት ዕለት የሚገኙ፣ ሙያዊ ብቃቱ ያላቸው፣ ከዩኒቨርሲቲው ፕሮጀክት ጽ/ቤት ጋር በመሆን የዕለት ከዕለት ችግር የሚፈቱ ከአቅም በላይ የሆነውን ደግሞ ከዋናው መስሪያ ቤት በመነጋገር መፍትሄ የሚሹ፣ ክፍያዎችን የሚያፋጥኑ፣ እና በወቅቱ



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

እንዲጠናቀቀቅ ትልቁን ሚና የሚጫወቱ የኮንስትራክሽን ድርጅት አማካሪ ባለሙያዎች ስለሆኑና እነዚህን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንዲመደቡ አሳስበዋል፡፡ በዩኒቨርሲቲው በየወሩ የግምገማ መድረክ ስለሚኖር እዚህ የሚኖረው የሳይት መሀንዲስ ሙሉ ሰዓቱን እዚህ በመሆን ሰራተኛውን አነቃንቆ የሚያሰራ የኮንስትራክሽን ድርጅቱን ሀብት በአግባቡ የሚጠቀም፣ ተግባብቶ የሚሰራ እና ሙያዊ ብቃት ያለው ሰው መመደብ ያስፈልጋል በማለት ፕሬዚዳንቱ አሳስበዋል፡፡

ባለአምስት ፎቅ የአስተዳደር ህንፃውን ለማሰራት በመቶ ሃያ አንድ ሚሊዮን ብር የፕሮጀክት ዋጋ ከፋሊንትስቶን ኢንጅነሪንግ ጋር እንዲሁም ባለሁለት ፎቅ የሆነ የመምህራንና ሰሠራተኞች መዝናኛን

ደግሞ በሀምሳ ሚሊዮን ብር የፕሮጀክት ዋጋ ከታምራት ተመስጌን ህንፃ ስራ ተቋራጭ ጋር የውል ስምምነት የተፈራረመ ሲሆን ሁለቱም ግንባታዎች በዋናው ግቢ የሚገነቡ ሁነው ግንባታው በስድስት መቶ የስራ ቀናት እንደሚጠናቀቀቅ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ተስፋሁን አበበ ገልፀዋል፡፡

እንደ አቶ ተስፋሁን ገለፃ የመማር ማስተማር ሂደቱን የተሳለጠ ለማድረግና ምቹ የስራ አካባቢ ለመፍጠር እነዚህ ግንባታዎች አስፈላጊ ናቸው፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳን የግንባታ ሁኔታውን የሚከታተሉ አማካሪ መሀንዲሶች ቢኖሩም ከእነርሱ ጋር በመሆን የግንባታ ሂደቱን በመከታተልና በመገምገም ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የግንባታ ግዜ እና የጥራት ሁኔታ እንዲጠናቀቁ የዩኒቨርሲቲው የፕሮጀክት ጽህፈት ቤት የበኩሉን እንደሚወጣ አሳስበዋል፡፡

## በሴት ተማሪዎች ላይ በሚታዩ ችግሮች እና የመፍትሄ ሃሳቦች ዙሪያ ውይይት ተደረገ

በሰለሞን አበበ





0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

ሴት ተመራቂ ተማሪዎች በሚከሰትባቸው ችግሮች ዙሪያ ውይይት ሲያደርጉ

**ደ/ማ/ዩ፡-** የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የስርዓተ ፆታ ኤች አይቪ ኤድስ እና አካል ጉዳተኞች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት በሴት ተማሪዎች ላይ በሚታዩ ችግሮች እና የመፍትሄ ሃሳቦች ዙሪያ ከተመራቂ ሴት ተማሪዎች ጋር ውይይት አደረገ፡፡

የውይይት መርሀ ግብሩን የመሩት ከእንግሊዝኛ ትምህርት ክፍል ተማሪ ፍሬህይወት ለገሰ፣ ከባዮሎጂ ትምህርት ክፍል ተማሪ ሀና በሻህ፣ ከኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል ተማሪ ፀደይ አባይነህ እና

ከኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ ማኔጅመንት ትምህርት ክፍል ተማሪ አቢሲኒያ ፈንታው ናቸው፡፡ የውይይቱ ዓላማ ሴት ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው እና በማህበረሰቡ ውስጥ በመማር ማስተማሩ፣ በአስተዳደሩ፣ በፆትዊ ትንኮሳ ወዘተ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን ለመለየት እና የመፍትሄ ሃሳብ በማስቀመጥ በየአመቱ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገቡ ሴት ተማሪዎች ትምህርታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች እንዳያቋርጡ እና ትምህርታቸውን ጨርሰው እንዲወጡ ለማድረግ ነው፡፡

በውይይት መርሀ ግብሩ ሴት ተማሪዎች እንደ ወንዶች ስኬታማ ሆነው ውጤታቸውን አስጠብቀው ትምህርታቸውን እንዳይጨርሱ የሚያደርጓቸው በራስ የመተማመን ችግር፣ እንችላለን የሚል እምነት በውስጣቸው ያለመሰነቅ፣ የስነልቦና ዝግጅት ለሚያጋጥማቸው ችግሮች አለማድረግ፣ የአማካሪ ሴት መምህራን ቢመደቡም ስራቸውን በአግባቡ ያለማከናወን፣ ሴቶች ከሴቶች አንድ ለአምስት ያለ መደራጀት ችግር፣ ለሴቶች ልዩ ቤተመጽሀፍት ያለመኖር፣ የሴቶች የኮምፒውተር ክፍል ያለመኖር፣ የፆታዊ ትንኮሳዎች መኖር፣ ሴቶች ለሴቶች እርስ በእርስ የመረዳዳት ችግር መኖር፣ ወንዶች ተማሪዎች ላይ በአሳይመንት፣ በፕሮጀክት ወዘተ ጥገኛ መሆን፣ በድፍረት ያልተረዱትንና ያልገባቸውን ትምህርት ያለመጠየቅ ችግር፣ የሴቶች ቱቶሪያል እና የድጋፍ አሰጣጥ አናሳ መሆን በውይይቱ በተሳታፊዎች የተነሱ ችግሮች ናቸው፡፡

የስርዓተ ፆታ ኤች አይቪ ኤድስና አካል ጉዳተኞች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ የውልሰው መላክ ዩኒቨርሲቲው ሊያደርጋቸው ይገባሉ ተብለው ለተነሱ ሃሳቦች በሰጡት መልስ የአንድ ለአምስት



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

የሴቶች እራሱን የቻለ አደረጃጀት መኖር ችግሮች በተሻለ መልኩ ለመቅረፍ ይረዳል የተባለውን በየትኛው አግባብ እንሂድ የሚለውን ለወደፊት የሚሠራበት ይሆናል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም በዩኒቨርሲቲው የሴቶች እራሱን የቻለ ላይበራሪ ባለመኖሩ በዩኒቨርሲው መብራት በሚጠፋበት ሰዓት ሴት ተማሪዎች ይተነኮሳሉ ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው በማደግ ላይ ያለ ዩኒቨርሲቲ ስለሆነ ለወደፊት የሴቶች የራሳቸው ላይ በራሪ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው መማር እንዲችሉ ለማድረግ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ሴቶች ለሴቶች እርስ በእርስ የመረዳዳት ባህል በማዳበር ዝቅተኛ ውጤት ያላቸውን ተማሪዎች ከትምህርት እንዳይባረሩ አስቀድሞ መተጋገዝ እና መረዳዳትን ችግሩን መቅረፍ ይገባል በማለት አሳስበዋል፡፡

## የህግ ትምህርት ቤት ለፍትህ አካላት ስልጠና ሰጠ

በሁሉንአየን ጋሻው



የስልጠናው ከፊል ገጽታ

ደ/ማ/ዩ፡- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርት ቤት ከማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር ከምስራቅ ጐጃም ዞን ለተውጣጡ የፍትህ አካላት በዩኒቨርሲቲው የመብሰቢያ አዳራሽ የሁለት ቀን ስልጠና ሰጠ፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶ/ር አራምዴ ፌጠነ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር እንደገለፁት ዳይሬክቶሬቱ ለተለያዩ የማህበረሰብ አካላት በተለያዩ ጉዳዮች የተለያዩ ስልጠናዎችን ሲሰጥ መቆየቱን አስታውሰው ይህ ስልጠናም ለፍትህ አካላት ሲሰጥ የቆየውን ለማጠናከርና ሰልጣኞችን ማነቃቂያ እንዲያገኙ ለማስቻልም የታሰበ ነው፡፡

ስልጠናው በዩኒቨርሲቲው የህግ ት/ቤት በመምህርነት እያገለገሉ ያሉና በፍትህ ስራም የተሻለ ልምድና ዕውቀት ያላቸው መምህራን የየራሳቸውን የመወያያ ጽሁፎች እንደሚያቀርቡና በጽሁፎቹም ተሳታፊዎች የነቃ ተሳትፎ በማድረግ በቂ ዕውቀትና የልምድ ልውውጥ ማድረግ የሚያስችል መሆኑን እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡

የህግ ት/ቤት ዲን የሆኑት አቶ መኩሪያው አለሜነው በበኩላቸው ባደረጉት ንግግር የስልጠናው ዓላማ የፍትህ ስራ በቀጥታ ማህበረሰቡን የሚመለከት በመሆኑ ማህበረሰቡን በአግባቡ ለማገልገል ደግሞ

የፍትህ አካላት ተገቢ የሆነ አሰራርን መከተል ስለሚገባቸው ይህን አስመልክቶ የእርስ በእርስ የዕውቀትና የልምድ ልውውጥ ለማድረግ ነው፡፡

ሰልጣኞች ከስልጠናው አዲስ ዕውቀትን እንዲያገኙ ታስቦ ሳይሆን የፍትህ ስራ ሲሰሩ የቆዩ በመሆናቸው በስራ ያጋጠሟቸውን ሁኔታዎች በመዳሰስ የእርስ በእርስ የልምድ ልውውጥ ለማድረግና ሰልጠኞች በስራ ላይ የቆየውን ዓዕምሮአቸውን ማነቃቃት እንዲችሉ ታስቦ የተዘጋጀ ነው ብለዋል፡፡

ለሁለት ቀናት በቆየው የፍትህ አካላት ስልጠና በተለያዩ ርዕሶች የህግ ትምህርት ቤት መምህራን በተመረጡ ርዕሶች ላይ የመወያያ ጽሁፎችን አቅርበዋል፡፡ "በመጀመሪያ ክርክር የፍርድ አሰጣጥ እና የፍርድ ቤቶች ስልጣን በኢትዮትያ፣ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን አለማቀፍ የሰባዊ መብቶች ድንጋጌዎች ለመተግበር የፍትህ ተቋማት ያሉባቸው እንቅፋቶች፣ Restorative Justice: gaps under the criminal justice system in Ethiopia፣ የኢትዮጵያ የህግ ማዕቀፎች ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ከመከላከል አንፃር ያላቸው ሚና እና ነፃ የህግ አገልግሎት ላይ የመነሻ ሃሳብ" በአቶ አያሌው አባተ፣ በአቶ ወ/ትንሳኤ ፈንቴ፣ በአቶ ምስጋናው ጋሻው፣ በአቶ ሃይሌ አንዳርጌ እና በአቶ ወ/ትንሳኤ ፈንቴ በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

በቀረቡት ሁሉም ጽሁፎች ላይ ተሳታፊዎች ጥያቄዎችን አቅርበው በአቀራቢዎቹ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፣ ሰፊ ውይይትም አድርገውባቸዋል፡፡

ስልጠናው በስራ ላይ የቆየውንና የነበረባቸውን የመዳከም ስሜት እንዳነቃቃቸውና የእርስ በእርስ ትውውቅና የልምድ ልውውጥ ማድረግ ያስቻላቸው መሆኑን ሰልጣኞች ጠቁመዋል፡፡ በመሆኑም በስልጠናው ያገኙትን ዕውቀትና ልምዳቸውን ተጠቅመው ማህበረሰቡን በተገቢው በማገልገል በማህበረሰቡ ዘንድ የፍትህን ጠቀሜታ የበለጠ እንዲገነዘቡት ለማስቻል እንደሚሰሩ እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው የጀመረውን ይህን አይነቱን ስልጠና አጠናክሮ በመቀጠል በማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት የበለጠ ማረጋገጥ የሀገሪቱን ልማት ለማረጋገጥ እንደሚገባው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

## Debre Markos University Graduates Students Colorfully

**Hulunayen Gashaw**




Dr. Tilaye Gete, DMU president, delivering speech

DMU:- Debre Markos University Graduates 2765 undergraduate and post graduates candidates trained in the regular and extension programs colorfully. On the graduation ceremony, Dr. Tilaye Gete, Debre Markos University President, states that education has pivotal roles in developing a country. Thus, the government has designed and implemented education policy, which could alleviate this problem since 1995. President added that the current graduation is the fruits of the policy and DMU would further strengthen the process of producing academically competent and ethically built citizens.




*Honorable Binalf Andualem, Amhara Regional State Deputy President And Education Office Head, Head of DMU Management Board Honored guest of the day delivering massages to the candidates.*

Mr. Binalf, on his side congratulates candidates, families and the university community for the successful graduation of this huge number of students. According to him producing competent manpower is the cradle of Ethiopia's renaissance and DMU is doing its level best in this regard.

On the graduation ceremony two honored guests were invited from DMU's Partner University in Vienna, Austria.



Professor Dr. Josef Glossl is a vice president for research and international research collaboration at the University Of Natural Resource And Life Science. Professor Josef Glossl expresses his appreciation for



**0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269** E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

DMU's endeavor in teaching learning and research activities. According to him his university is committed to strengthen its partnership with DMU. It is also known that Dr. Reinfried Mansberger, who is a Director of the Tripartite Project among DMU, University of Natural Resource and Life Sciences and Technical University of Vienna.

On the occasion, an award was given for best scoring students at Department, College and University level.





Finally, DMU presents the special Prize of the year to Mr. Solomon Girmay, who has shown an exceeding performance in the campus Beautification and cleaning process, by awarding him a motorcycle worthy of 45,000 Ethiopian birr.







0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication